dc paid family leave

DISTRICT OF COLUMBIA DEPARTMENT OF EMPLOYMENT SERVICES

# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት
# ዲፓርትመንት ኦፍ ኢምፕሎይመንት ሰርቪስ

## ማስታወቂያ ለሰራተኞች
## የዲሲ የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ የሚመለከት መረጃ

ቀጣሪዎ በዲሲ የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ህግ ይመለከተዋል?፣ ይህም በህጉ መሰረት ሽፋን የሚሰጣቸው ሰራተኞች የወላጅ፣ የቤተሰብ፣ የህክምና እና ለቅድመ ወሊድ ዝግጅቶች የሚከፈሉበት ዕረፍት ጊዜ ይሰጣል። የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ፕሮግራም በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ቢሮ ድህረ ገጽን dcpaidfamilyleave.dc.gov ይጎብኙ።

### ሽፋን የሚያገኙ ሰራተኞች

በሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ፕሮግራም ስር ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት፣ በዲሲ ውስጥ ሽፋን ላለው ቀጣሪ መስራት አለብዎት። ሽፋን ያለው ሰራተኛ መሆንዎን ለማወቅ፣ ቀጣሪዎን መጠየቅ ወይም የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ቢሮን ከስር በተቀመጠው መረጃ አማካይነት ማነጋገር ይችላሉ። በሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ፕሮግራም ሽፋን ያልዎት ከሆነ አሰሪዎ ሊነግርዎት ይገባል። በተጨማሪም፣ ቀጣሪዎ በእነዚህ ሶስት (3) ጊዜያት ስለ የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ፕሮግራም መረጃ መስጠት ይጠበቅበታል።

1. በተቀጠሩበት ጊዜ;
2. ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ፤ እና
3. በሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ፕሮግራም ስር ለጥቅማጥቅሞች ብቁ የሚሆን ፈቃድ ለቀጣሪዎ ከጠየቁ።

### ሽፋን የሚያገኙ አጋጣሚዎች

አራት (4) ዓይነት የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ጥቅሞች አሉ፦

1. የወላጅ ፈቃድ - በዓመት ውስጥ እስከ 12 ሳምንታት ያኽል አዲስ የተወለደ ልጅ የሚያካትት ጥቅማጥቅሞችን መቀበል፤
2. የቤተሰብ ፈቃድ - በዓመት ውስጥ እስከ 12 ሳምንታት ያኽል የቤተሰብ አባልን ለመንከባከብ ጥቅማ ጥቅሞችን መቀበል፤
3. የሕክምና ፈቃድ - በዓመት ውስጥ እስከ 12 ሳምንታት ድረስ ለራስዎ ከባድ የጤና ሁኔታ ጥቅማ ጥቅሞችን ያገኛሉ፤ እና
4. የቅድመ ወሊድ ፈቃድ - በዓመት ውስጥ እስከ 2 ሳምንታት ለቅድመ-ወሊድ ሕክምና እንክብካቤ ጥቅማጥቅሞችን ያገኛሉ።

### የመጨረሻው ከፍተኛ የፍቃድ መብት

እያንዳንዱ የእረፍት አይነት የራሱ የብቃት ህጎች እና በዓመት ውስጥ ጥቅማጥቅሞችን በሚያገኙበት ጊዜ የራሱ የሆነ ገደብ አለው። ለማንኛውም የወላጅ፣ የቤተሰብ እና የህክምና ፈቃድ ባንድ ላይ ከፍተኛው የእረፍት መጠን 12 ሳምንታት ነው። ይሁን እንጂ የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ለሚወስዱ እርጉዝ. ሴቶች በተለየ መልኩ ይታያል። ነፍሰ ጡር እናቶች በእርግዝና ወቅት ለ 2 ሳምንታት የቅድመ ወሊድ እረፍት እና ከወለዱ በኋላ ደግሞ ለ 12 ሳምንታት የወላጅ ፈቃድ፣ ቢበዛ ለ 14 ሳምንቶች ብቁ ይሆናሉ።

### ለጥቅማጥቅሞች ማመልከት

ለጥቅማጥቅሞች ብቁ የሚሆን ክስተት አጋጥሞዎት ከሆነ፣ መሆንዎን ካረጋገጡ ጀምሮ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማመልከት አለብዎት። ለጥቅማጥቅሞች ስለማመልከት የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ቢሮ ድረገጽ በሆነው dcpaidfamilyleave.dc.gov የበለጠ ማወቅ ይችላሉ።

### የጥቅጥቅም
### መጠኖች

የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ጥቅማጥቅሞች አሰሪዎ በከፈለዎት ደሞዝ እና ለየዲፓርትመንት ኦፍ ኢምፕሎይመንት ሰርቪስ የተደረው የክፍያ ሪፖርት የሚመሰረት ናቸው። ደሞዝዎ በስህተት ሪፖርት ተደርጓል ብለው ካመኑ፣ የእርስዎን ትክክለኛ ደሞዝ ማረጋገጫ የማቅረብ መብት አለዎት። ሰአት ያለው ከፍተኛው ሳምንታዊ የጥቅማጥቅም መጠን $1,118 ነው።

### የሰራተኛ ጥበቃ

የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ቢሮ ለዲሲ ከስራ እረፍት ለሚወስዱ የዲስ ሰራተኞች ምንም አይነት የስራ የስራ ከለላን አይመለከትም። ነገር ግን፣ በዲስትሪክቱ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) በሚተዳደረው ሕግ እና መመሪያ መሠረት አንዳንድ የሥራ ጥበቃዎች ሊያገኙ ይችላሉ።

በአለምአቀፍ የሚከፈል ፈቃድ ህግ መሰረት፣ የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ቢሮ የሚከተሉትን ማሳወቅ ይጠበቅበታል።

1. የፈቃድ ጥቅማጥቅሞችን በመጠየቅ፣ በማመልከት ወይም በመጠቀማቸው ምክንያት ሽፋን ባለው አሠሪ ሽፋኝ ባለው ሠራተኛ ላይ የሚወስደው የበቀል እርምጃ የተከለከለ መሆኑን፤
2. ከ 20 በታች ሰራተኞች ያሉት ሽፋን ባለው ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሰራተኛ በዚህ ሕግ መሰረት የሚከፈል ፈቃድ ለመውሰድ ከወሰነ ከስራ ከለላ ሊደረግለት እንደማይችል፤ እና
3. ሰራተኞች የሚከፈል ፈቃድ በመጠየቃቸው፣ በማመልከታቸው ወይም በመጠቀማቸው ምክንያት የብቀላ ሰለባ እንደሆኑ ከተሰማቸው ለ ዲሲ ሰበዊ መብቶች ቢሮ (ኦ ኤች አር) ቅሬታ የማቅረብ መብት አላቸው።

ስለ (ኦ ኤች አር) እና የስራ ከለላን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የሚከተለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ፡ ohr.dc.gov።

ስለ የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን የሚከፈል የቤተሰብ ፈቃድ ቢሮ ድህረ ገጽን በ dcpaidfamilyleave.dc.gov ይጎብኙ፣ በ 202-899-3700 ይደውሉ፣ ወይም ወደ does.opfl@dc.gov. ኢሜይል ይላኩ።